4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

# በስደት ከሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት የተሰጠ መግለጫ

## ፍርዱ ኢ-ፍትሃዊ እና ለሰላምና ለአንድነት እንቅፋት ነው።

በእግዚአብሔር አጋዥነትና ረዳትነት ነጻነቷንና አንድነቷን ጠብቃ የኖረችው ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ፥ ያለፉትን ሁለት ሺህ ዓመታት (ሚሊኒየም) ፈጽማ ሦስተኛውን በምስጋና ለመቀበል በዋዜማ ላይ ባለችበት ወቅት፥ የነጻ ፕሬስ አባላትን፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችን፥ የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾችን በሞት ሊያስቀጣ በሚችል ፍርድ ጥፋተኞች መሆናቸውን ሥልጣኑን በያዘው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያለው ፍርድ ቤት አውጇል።

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ባወጣቸው መግለጫዎች እንደገለጠው፥ የፍርድ ሂደቱ ዓለም አቀፋዊ የሰብኣዊ መብት አንቀጾችን የጣሰ፣ ሚዛናዊነትና ግልጽነት የጎደለው ሲሆን ክሱም ሆን ተብሎ በፖለቲካና በኅሊና እስረኞች ላይ የተለጠፈ ስለሆነ ድርጊቱን በጽኑ ያወግዛል። ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ አቋም በመላው ዓለም በሚገኙ የሰብኣዊ መብት ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ የሙያ ማኅበራት እና ኅሊና ባላቸው መንግሥታት ጭምር የተደገፈ ነው።

ታሪካዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በፍትሕና በእውነት ጎዳና ለመምራት ከጌታና ከሐዋርያት ደግሞም ከአበው አደራውን የተቀበለው ቅዱስ ሲኖዶስ በነጻ ፕሬስ አባላት፣ በፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና እና በሰብኣዊ መብት ተሟጋቾች ላይ የተሰጠው ፍርድ ለሀገር አንድነትና ሰላም እንቅፋትና ሀገራችንን ወደ በለጠ የእርስ በእርስ ግጭት የሚመራ ስለሆነ ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖች ሁሉ ወደ እርቅና ወደ ሰላም እንዲመጡ ጥሪ በማቅረብ፥

1. የታሰሩት የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች በሙሉ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይእንዲፈቱ፤

2. የመሰብሰብና የመናገር መብት ከሰው ልጆች የማይገሰስ ነጻነታቸው ስለሆነ ያለፈውን ምርጫ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ የወጡትን ኢትዮጵያውያን የገደሉና አካለ ጎደሎ ያደረጉ የጸጥታ ኃይሎችና ትእዛዝ ያስተላለፉ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በኃላፊነት እንዲጠየቁና በሥልጣን ያለውም ፓርቲ ኃላፊነቱን ተቀብሎ በይፋ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠይቅ፤

3. በወቅቱ በነበረው አለመረጋጋት ከየቦታው ተወስደው የት እንደደረሱ ያልታወቁ ልጆቻችን በሕይወት መኖራቸው ወይም መገደላቸው ለቤተሰቦቻቸው እንዲገለጥ፤

4. በአጠቃላይ ከምርጫው ጋር በተያያዘ የተነሱትን ግጭቶች የሚመረምር ገለልተኛ የሆነ አካል ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችና የሕግ ባለሙያዎች ባሉበት እንዲቋቋም፤

5. ሀገራችን ኢትዮጵያ በእውነተኛ ፍትሕና በሃይማኖታዊ ሥርዓት የታወቀች፤ ቤተ ክርስቲያኒቱም እውነትን በማስተማርና ለእውነተኛ ፍትህ የቆመች መሆኗ የሚነገርላት ሀገር ሆና ሳለች፥ እንደዚህ ያለ ኢ-ፍትሓዊ ደርጊት ሲፈጸም ያለፈውን ታሪኳን ሁሉ የሚደመስስ በመሆኑ እውነተኛ የፍትሕ ሰዎችና የታሪክ መዝጋቢዎች ይህን ድርጊት ለማስቆም ታሪካዊ ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ፤

6. የቤተ ክርስቲያንዋ ልጆች የሆናችሁ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያን ሰላም የምትሹ በሙሉ ይህንን ከሕግ ውጭ የሆነውን ይህንን ፖለቲካዊ ፍርድ የወሰኑ ግለሰቦች አካሄድ ለማንም ለምንም የማይበጅ መሆኑን ተገንዝባችሁ እግዚአብሔር ማስተዋሉን እንዲሰጣቸው በጸሎት ወደ ፈጣሪ አምላክ እንድትለምኑ፤

7. በፍትህ ጉድለት ምክንያት እስር ቤት ተጥለው ለሚሰቃዩ ወገኖቻችን ብርታት ይሆናቸው ዘንድ፤ ቤተሰቦቻቸውንም ይደግፍ ያጽናና ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸሎታችሁን እንድታቀርቡ፤

8. በዓለም ዙሪያ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የምናከብረው የአዲሱ ሚሊኒየም ክብረ በዓል አዛውንቶቻችንንና ምሁሮቻችንን እስር ቤት አጉረን በጭካኔና በመርገም የምናከብረው ሳይሆን በአንድነት በሰላምና በፍቅር የምናከብረው እንዲሆን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

*እግዚአብሔር አምላክ ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ሰላምን ይስጥልን።*
*በእስራት ያሉትንም ቤተሰቦቻቸውንም ጽናቱን ይስጥልን።*